## የቴሌኮሙኒኬሽን መሳሪያዎች የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ተገልጋዮች ማሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

ለግለሰቦች/ቀጥታ ተጠቃሚ ደርጅቶች፣

1. የመሳሪያው አይነትና ሞዴል በማመልከቻቸው ላይ በትክክል መሞላት ይኖርበታል
2. መሳሪያው ጉምሩክ ለመድረሱ ማረጋገጫ ከጉምሩክ ቀሪ ለተደረጉ ዕቃዎች የሚሰጥ መረጃ መቅረብ ይኖርበታል
3. ስለ መሳሪያው ተገቢ የቴክኒክ ዝርዝሮችና አጠቃቀሙን የሚያሳይ የቴክኒክ ማኑዋል መቅረብ ይኖርበታል

ለአስመጪዎች፣

1. የመሳሪያው አይነትና ሞዴል በማመልከቻቸው ላይ በትክክል መሞላት ይኖርበታል
2. መሳሪያው ጉምሩክ ለመድረሱ ማረጋጫ ከጉምሩክ/ከኤርፖርት፣ ከካርጎ ተርሚናል፣ ከፖስታ ቤት ወይም ከላጋር/ቀሪ ለተደረጉ ዕቃዎች የሚሰጥ መረጃ መቅረብ ይኖርበታል
3. መሣሪያው የተገዛበት ኢንቮይስ፣ መሳሪያው የተጓጓዘበት የአየር ወይም የባህር ማስጫኛ ሰነድ
4. ከኤጀንሲው የተሰጠ የቴሌኮሙኒኬሽን ተርሚናል ዕቃዎቸ ጥገና ፈቃድ ሊኖር ይገባል
5. ስለ መሳሪያው ተገቢ የቴክኒክ ዝርዝሮችና አጠቃቀሙን የሚያሳይ የቴክኒክ ማኑዋል መቅረብ ይኖርበታል

## የቴሌኮሙኒኬሽን መሳሪያዎች የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት ተገልጋዮች የሚከተሉት ሂደት

| የሚከናወን ተግባር | የሚፈጀው ጊዜ |
|---|---|
| ለፈቃድ ጥያቄ ያዘጋጁትን ሰነዶች ለፈቃድ መስጫ ኦፊሰር ያቀርባሉ፣ ኦፊሰሩ ሰነዶቹን አጣርቶ የተሟላ ከሆነ የፈቃድ ካርድ ያዘጋጅሎታል፣ መረጃውንም ወደ ዳታ ቤዝ ውስጥ ያስገባል | ለስልክ፣ ፋክስ እና ኢንተርኔት ሪሴል እና ለቴሌሴንተር ፈቃድ 15 ደቂቃ<br><br>ለውስጥና ውጭ ኬብል ስራ እና ለማዞሪያና ለተርሚናል እቃዎች ጥገና ፈቃድ 30 ደቂቃ |
| ለገንዘብ ተቀባይ ክፍያ ፈፅመው የፈቃድ ካርዱ ላይ ማህተም በማስደረግ ከክፍያ ደረሰኝ ጋር ይቀበላሉ | ለሁሉም የፈቃድ ዓይነቶች 10 ደቂቃ |
| ድምር | ለስልክ፣ ፋክስ እና ኢንተርኔት ሪሴል እና ለቴሌሴንተር ፈቃድ 25 ደቂቃ<br>ለውስጥና ውጭ ኬብል ስራ እና ለማዞሪያና ለተርሚናል እቃዎች ጥገና ፈቃድ 40 ደቂቃ |

ማሳሰቢያ:-

1. ባልተሟሉ መረጃዎች የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ለማግኘት የሚያመለክት ተገልጋይ የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ኦፊሰሮች ያልተሟሉ መረጃዎችን ለማግኘት ኢንተርኔት በመጠቀም ተጨማሪ የማጣራት ስራዎችን ማካሄድ ስለሚኖርባቸው የስራ ሂደቱ ከሚወስደው ጊዜ በላይ ሊቆይባቸው ወይም የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫውን ለማግኘት የማይችሉበት ሁኔታዎች ሊፈጠሩ ይችላሉ። በመሆኑም ተገልጋዮች መያያዝ ያለባቸው መረጃዎችን አሟልተው ቢቀርቡ ለአገልግሎት አሰጣጡ ቅልጥፍና ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።
2. በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የተስተዋለ ችግር ካለ ተገልጋይ ቅሬታውን በቅሬታ መስጫ ፎርም መሙላት ወይም በአካል በመቅረብ ለደረጃዎችና የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ ዳይሬክተር ሁለተኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 209 ወይም ለስነምግባር መኮንን አራተኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 403 በቀጥታ ማቅረብ ይቻላል።

## የስልክ፣ ፋክስ እና ኢንተርኔት ሪሴል፣ የቴሌሴንተር ፈቃድ፣ የውስጥና ውጭ ኬብል ስራ እና የማዞሪያና የተርሚናል እቃዎች ጥገና ፈቃድ ለማውጣት ተገልጋዮች ማሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታ

### ለስልክ፣ ፋክስ እና ኢንተርኔት ሪሴል እና ለቴሌሴንተር ፈቃድ

ሀ. የዋና ምዝገባ የምስክር ወረቀት፣ የንግድ ማህበር ከሆነ የመመስረቻ ፅሁፍና መተዳደሪያ ደንብ

ለ. ከኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን ጋር የተደረገ የሪሴል ውል

ሐ. የታደሠ የቀበሌ የነዋሪነት መታወቂያ ወይም ፓስፖርት

መ. አገልግሎቱ የሚሠጥበት አድራሻ

ሠ. ሁለት ጉርድ ፎቶ ግራፍ፣

### ለውስጥና ውጭ ኬብል ስራ እና ለማዞሪያና የተርሚናል እቃዎች ጥገና ፈቃድ

ሀ. የዋና ምዝገባ የምስክር ወረቀት፣ የንግድ ማህበር ከሆነ የመመስረቻ ፅሁፍና መተዳደሪያ ደንብ

ለ. የባለሞያዎች ብዛት፣ የትምህርትና የሥራ ልምድ ማስረጃ እንዲሁም ባለሙያዎቹ ከድርጅቱ ባለቤት ወይም ንግድ ድርጅቱ ጋር ያደረጉት የሥራ ውል ማስረጃ ዋናውን ከፎቶ ኮፒ ጋር፣

ሐ. የመሳሪያዎች (tools) እና የመመርመሪያ መሳሪያዎችን (instruments) አይነትና ብዛት የሚገልፅ ዝርዝር መረጃ፣

መ. የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት

ሠ. ሁለት ጉርድ ፎቶ ግራፍ

## የስልክ፣ ፋክስ እና ኢንተርኔት ሪሴል፣ የቴሌሴንተር ፈቃድ፣ የውስጥና ውጭ ኬብል ስራ እና የማዞሪያና የተርሚናል እቃዎች ጥገና ፈቃድ ለማግኘት ተገልጋዮች የሚከተሉት ሂደት

| የሚከናወን ተግባር | የሚፈጀው ጊዜ |
|---|---|
| ለፈቃድ ጥያቄ ያዘጋጁትን ሰነዶች ለፈቃድ መስጫ ኦፊሰር ያቀርባሉ፣ ኦፊሰሩ ሰነዶቹን አጣርቶ የተሟላ ከሆነ የፈቃድ ካርድ ያዘጋጅሎታል፣ መረጃውንም ወደ ዳታ ቤዝ ውስጥ ያስገባል | ለስልክ፣ ፋክስ እና ኢንተርኔት ሪሴል እና ለቴሌሴንተር ፈቃድ 15 ደቂቃ<br><br>ለውስጥና ውጭ ኬብል ስራ እና ለማዞሪያና ለተርሚናል እቃዎች ጥገና ፈቃድ 30 ደቂቃ |
| ለገንዘብ ተቀባይ ክፍያ ፈፅመው የፈቃድ ካርዱ ላይ ማህተም በማስደረግ ከክፍያ ደረሰኝ ጋር ይቀበላሉ | ለሁሉም የፈቃድ ዓይነቶች 10 ደቂቃ |
| ድምር | ለስልክ፣ ፋክስ እና ኢንተርኔት ሪሴል እና ለቴሌሴንተር ፈቃድ 25 ደቂቃ<br>ለውስጥና ውጭ ኬብል ስራ እና ለማዞሪያና ለተርሚናል እቃዎች ጥገና ፈቃድ 40 ደቂቃ |

**ማሳሰቢያ:**

1. ባልተሟሉ መረጃዎች የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች ፈቃድ ማግኘት አይቻልም።
2. በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የተስተዋለ ችግር ካለ ተገልጋይ ቅሬታውን በቅሬታ መስጫ ፎርም በመሙላት ወይም በአካል በመቅረብ ለፈቃድና ኢንስፔክሽን ዳይሬክተር ሁለተኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 201 ወይም ለስነምግባር መኮንን አራተኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 403 በቀጥታ ማቅረብ ይቻላል።